የሰ/መ/ቁ. 31721

ጥቅምት 25 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ብዙነሽ ኃ/ዮሐንስ - ጠበቃ መድሕን መሐሪ ቀረበ፡፡

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ስንታየሁ እሸቱ - በሌለችበት

መዝገቡን መረምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ ከውል ውጪ የደረሰ ኃላፊነትን መሠረት አድርጎ የቀረበ የካሣ ክፍያ ጥያቄን /ክርክር/ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በሶማሌ ብ/ክ/መ/ በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ ተጠሪ ስትሆን በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተችውም የምትወልደው ልጅዋ ሦስት ሕፃናት ልጆቼን አርዶ ስለገደለብኝ በእናትነትዋ ካሣ ልትከፍለኝ ይገባል በማለት ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠችው መልስ ጉዳዩ በፈጸመው ድርጊት ኃላፊ የምሆንበት የሕግ ምክንያት የለም፤ መከሰሴም ያለአግባብ ነው፡፤ በማለት ስለመከራከርዋ ከመዝገቡ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ክሱን ያስተናገደው ፍ/ቤትም የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር ከሰማ በኋላ ተከሣሽ ላደረሰው ጉዳት ኃላፊ ናት በመሆኑም በጠቅላላው ብር 35000(ሰላሳ አምስት ሺህ) ካሣ ለከሣሽ ትክፈል በማለት ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ይህን ውሣኔ በመቃወም ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማለትዋ በዚህ ይግባኝ ደረጃም ክርክሩ ተሰምቶአል፡፡ በመቀጠልም ፍ/ቤቱ በከፍተኛው ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን ውሣኔ በማሻሻል አመልካች ብር 78000(ሰባት ሺህ ስምንት መቶ) ካሣ እንድትከፍል ወስኖአል፡፡ በጨረሻም የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ከአመልካች በቀረበለት አቤቱታ መነሻነት ክርክሩን ከሰማ በኋላ በጠ/ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ አጽንቶአል፡፡ የአሁኑ አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ሐምሌ 6 ቀን 1999 ዓ.ም. በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ተጠሪ በተደረገላት ጥሪ መሠረት ባለመቅረብዋ ክርክሩ የተሰማው እሷዋ በሌለችበት ነው፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች ደረሰ ለተባለው ጉዳት ኃላፊ የምትሆንበትና ካሣ የምትከፍልበት የሕግ ምክንያት አለ ወይ? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ ባጭሩ እንደተመለከተው አመልካች የተከሰሰችው እና በመጨረሻም ኃላፊ ነሽ የተባለችው እርስዋ በፈጸመችው ድርጊት ጉዳቱን አድርሳለች በሚል አይደለም፡፡ ጉዳቱን አድርሷል የተባለው የእሷ ልጅ የሆነው ሰው ነው፡፡ እርሱም ልጆቹን ከገደለ በኋላ ራሱንም እንዳጠፋ በተጠሪ ክስ ተገልጾአል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሰውየው አካለ መጠን የደረሰና ዕድሜውም ከ40 ዓመት በላይ እንደነበረ በክርክሩ ተመልክቶአል፡፡ ተጠሪ ክሱን የመሠረተችው በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2125 የተመለከተውን ድንጋጌ በመጥቀስ ሲሆን ይህ ድንጋጌ የሚያመለክተው በአባት አላፊነት ምትክ ሆነው ስለሚጠየቁት ሰዎች ነው፡፡ ድንጋጌው የሚገኘው "ለሌላ ሰው ተግባር አላፊ ስለመሆን" በፍትሐብሔር ሕጉ በአንቀጽ 13 በምዕራፍ 1 /ከውል ውጪ ስለሚደርስ አላፊነት/ በሚለው በክፍል 4 ስር ነው፡፡ ከቁጥር 2125 በፊት ያለው ቁ. 2124 አካለ መጠን ያላደረሰ ልጅ አላፊነትን የሚያስከትል ሥራ የሠራ እንደሆነ በፍትሐብሔር በኩል ለተሠራው ሥራ አላፊ የሚሆነው አባት እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ቁጥር 2125 ደግሞ አባት በሌለ ጊዜ በሱ ምትክ ኃላፊ የሚሆኑትን በተመለከተ

የሚደነግግ ነው፡፡ ከእነዚህ ሰዎች መካከል አንዷ የልጁ እናት እንደሆነችም በዚሁ  ቁጥር 2125/ሀ/ ተመልክቶአል፡፡ እንግዲህ እንደተጠሪ ክስ አመልካች ኃላፊ ልትሆን ትችል የነበረው ጉዳቱን አድርሷል /የተጠሪን ልጆች ገድሎአል/ የተባለው ሰው አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ቢሆን ነበር፡፡ ይህ ግን በተጠሪ በኩል አልተረጋገጠም፡፡ ጉዳት አድራሹ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ነው የሚል በተጠሪ ክስም ሆነ ክርክር አልተነሳም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም ቢሆኑ ጉዳት አድራሹ ሰው ዕድሜው ከ40 ዓመት በላይ የነበረ እና በኔም ስር የሚተዳደር ያልነበረ ነው የሚለውን የአመልካችን ክርክር ከመመዝገብ አልፈው በእርግጥ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ነበር አላሉም፡፡ ይህም የሚያመለክተው ፍ/ቤቶቹ አመልካችን ኃላፊ ያደረጉዋት ኃላፊ የምትሆንበት የሕግ ምክንያት ሳይኖር እንደሆነ ነው፡፡ ከዚህ የተነሣም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በሶማሌ ብ/ክ/መ/ በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ እና በዚህ ውሣኔ ላይ በቀረበው ይግባኝ እና አቤቱታ ማስረጃነት በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት እና ሰበር ችሎት በመ/ቁ. **GM**181/98 ሰኔ 28 ቀን 98 ዓ.ም. እና በመ/ቁ. 09/99 ሚያዝያ 13 ቀን 1999 ዓ.ም. የተሰጡት ውሣኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1 መሠረት ተሸረዋል፡፡
2. አመልካች ደረሰ ለተባለው ጉዳት ኃላፊ የምትሆንበትም ሆነ ካሣ የምትከፍልበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት ወስነናል፡፡
   መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ